| | |
|---|---|
| ዐይነት ፤ | ርእስ ፡ አንቀጽ ። |
| ርእስ ፤ | "እምብዛ ፡ ብልኃት ፡ ..." |
| ደሆሲ ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ። |
| ዕለት ፤ | መስከረም ፡ 2016 ፡ ዓ.ም. ። |
| ዝግጅት ፤ | ፍጹም ። |
| መጽሔት ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፥ ቍ.2016-001 |
| ማስታወሻ ፤ | |
| ማሳሰቢያ ፤ | |

# ርእስ ፡ አንቀጽ ።

editorial | éditorial | اِفْتِتاحي

# "እምብዛ ፡ ብልኀት ፡ ..."



ኢትዮጵያን ፡ ለኹለት ፡ ከፍለው ፡ የተቀራመቷት ፡ የኢ..ፌ.ዴ.ሪ. ፡ ቅሬታ ፡ ይዘት ፡ እና ፡ የ"ሻዕቢያ" ፡ ክሽፍ ፡ ይዘት ፥ ከ 33 ፡ ዓመታት ፡ ውንብድና ፡ በኋላ ፡ ፍጻሜያቸው ፡ እንሆ ፡ ተቃርቧል ። ባንድ ፡ ወገን ፥ ከመቼውም ፡ የበለጠ ፡ የሕዝብ ፡ ዐመፃ ፡ በውስጥም ፡ በውጭም ፡ ተጠናክሮባቸዋል ፤ እስር ፡ ቤቶቻቸው ፡ ኸሉ ፡ በነጻነት ፡ ታጋዮች ፡ ተሞልተዋል ፥ የሚሰደደውም ፡ ነዋሪ ፡ ቍጥር ፡ ጨምሯል ። በሌላው ፡ ወገን ፥ ኹለቱ ፡ የውንብድና ፡ ይዘቶች ፡ ከዕለት ፡ ወደ ፡ ዕለት ፡ የሚባባስ ፡ የመዛል ፡ ኹኔታ ፡ ስለታየባቸው ፥ ሀገር ፡ ኢትዮጵያን ፡ የማፈራረስ ፡ ተልእኳቸውን ፡ በጥድፊያ ፡ ለመጨረስ ፡ ተመካክረው ፡ ተታግተዋል ። የሕዝብ ፡ ዐመፃን ፡ ለማፈንም ፡ ኾነ ፡ የሤራቸውን ፡ ክንዋኔ ፡ ለማፋጠን ፡ ሲፍጨረጨሩ ፡ ግን ፥ በብልኀት ፡ ላይ ፡ ብልኀትን ፡ እየጨመሩ ፡ የሚፈጽሟቸው ፡ ስሕተቶች ፡ እና ፡ ጥፋቶች ፡ ተደማምረው ፡ የባሰውን ፡ እተወሳሰበ ፡ የጥፋት ፡ አዙሪት ፡ ውስጥ ፡ ወድቀዋል ።

መንደር ፡ ገነን ፡ ዐቢይ ፡ አሕመድ ፥ ከምዕራቡ ፡ እና ፡ ከዐረቡ ፡ ዓለም ፡ አገኘዋለኹ ፡ በሚሉት ፡ ንዋያዊም ፡ መባሕታዊም ፡ መረጃዊም ፡ ጸጥታዊም ፡ ጦራዊም ፡ ስንቃዊም ፡ ድጋፍ ፡ ተማምነው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ ባስነሡት ፡ ግልጽ ፡ ጦርነት ፡ ምክንያት ፥ ከዐዲስ ፡ አበባ ፡ የ 30 ፡ ኪሎሜትር ፡ ዙሪያ-ገባ ፡ ግዛትን ፡ እና ፡ የገጠር ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ከተሞችን ፡ ከመቈጣጠር ፡ ሌላ ፡ አብዛኛዎቹ ፡ የሀገሪቱ ፡ ግዛቶች ፡ እንደማይገዙላቸው ፡ ኾነው ፡ ሸፍተውባቸዋል ። ማእከላዊውን ፡ መንግሥት ፡ ማላላት ፡ ከተልእኳቸው ፡ አንዱ ፡ ቢኾንም ፡ ቅሉ ፥ የቍጥጥር ፡ ልጓሙ ፡ አለጊዜው ፡ ከእጃቸው ፡ ፈጽሞ ፡ ያመለጠ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ የውንብድና ፡ አገዛዛቸውን ፡ ከባድ ፡ ዋጋን ፡ ያስከፍለዋል ። **የፋኖ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ንቅናቄ** ፡ የመላውን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ድጋፍ ፡ አግኝቷል ፤ ከዕለት ፡ ወደ ፡ ዕለትም ፥ በመሣሪያም ፡ በሰው ፡ ኀይልም ፡ ባደረጃጀትም ፡ እየዳበረ ፡ ስለ ፡ ኼደ ፥ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ አብዛኛዎቹን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ክፍለ ፡ ሀገሮች ፡ ሊቈጣጠርና ፡ የወረዳ ፡ አስተዳደሮችን ፡ ሊመሠርት ፥ ዐዲስ ፡ አበባንም ፡ በሕዝባዊ ፡ ማዕበል ፡ አጥለቅልቆ ፡ ሊይዛት ፡ ይችላል ። የፋኖን ፡ ግሥጋሤ ፡ ሊያውኩ ፡ እና ፡ ሊገቱ ፡ የሚችሉ ፡ በፋኖ ፡ ውስጥ ፡ የተሰገሰጉ ፡ ሠርጎ-ገቦች ፡ መኖራቸው ፡ ቢታወቅም ፡ ቅሉ ፥ ሕዝባዊ ፡ ማዕበሉን ፡ ለመቀልበስም ፡ ኾነ ፡ ለመቀየስ ፡ ዐቅምንም ፡ ብልኀትንም ፡ ተሰሚነትንም ፡ አያገኙም ፤ ቢሞክሩትም ፡ እንኳ ፥ የሚፋፋመው ፡ ትግል ፡ እያበጠረ ፡ እና ፡ እየመዘረጠ ፡ ያስወግዳዋቸል ። ይህንም ፡ ዐልፈው ፥ እስከመሸጋገሪያ ፡ መንግሥት ፡ ምሥረታ ፡ ድረስ ፡ ተሹለክልከውም ፡ እንኳ ፡ እሥልጣኑ ፡ ሰገነት ፡ ላይ ፡ ፊጥ ፡ ቢሉ ፥ እንደቀደመው ፡ ዘመን ፡ የሚታለልላቸውም ፡ ኾነ ፡ የሚታገሣቸው ፡ ትውልድ ፡ አያገኙምና ፥ አይሰነብቱም ።

*"ያማርኛ ፡ ሙዚቃን ፡ መስማት ፡ ክልክል ፡ ነው ! ፡ ..."* ፥ *"ጤፍ ፡ ሣር ፡ ነው ፤ ጤፍን ፡ አትብሉ ! ፡ ..."* ፥ *"ኢትዮጵያን ፡ የመቶ ፡ ዓመት ፡ የቤት ፡ ሥራ ፡ ሰጥተናታል ፡ ..."* ፡ ሲሉ ፡ የነበሩ ፤ ከማለትም ፡ ዐልፈው ፥ በ 1980-3 ፡ ዓ.ም. ፡ በአሶሳ ፡ እና ፡ በኤርትራ ፡ በረሓ ፥ ከሕ.ወ.ሐ.ት. ፡ ጋራ ፡ ተመሳጥረው ፥ ሀገራውያን ፡ ኢትዮጵያውያንን ፡ በገፍ ፡ ያስጨፈጨፉ ፡ መንደር ፡ ገነን ፡ ኢሳይያስ ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፥ ዛሬ ፡ ደግሞ ፥ ከመንደር ፡ ገነን ፡ ዐቢይ ፡ አሕመድ ፡ ጋራ ፡ ተመሳጥረው ፥ አረመኔውን ፡


©ኢ..ሀ.ሥ.አ. ፥ 2016 ፡ ዓ.ም. ።

ኦ.ነ.ግ. ፡ አስታጥቀው ፡ የንጹሓን ፡ ኢትዮጵያውያንን ፡ ደም ፡ ያላፈሰሱ ፡ ይመስል ፥ እንሆ ፥ ለማዘናጋት ፡ ሲሉ ፥ የበግ ፡ ለምዳቸውን ፡ አጥልቀው ፡ የ"ዐማራ" ፡ ተቈርቋሪ ፡ መስለው ፡ ለመጨረሻው ፡ ሤራቸው ፡ ብቅ ፡ ብለዋል ።

የሚቀጥሉት ፡ ሳምንታት ፡ መንደር ፡ ገ̇ነን ፡ ዐቢይ ፡ አሕመድ ፡ እና ፡ መንደር ፡ ገ̇ነን ፡ ኢሳይያስ ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፡ የሚያረዱን ፡ የሴራቸው ፡ የመደምደሚያ ፡ ሸር ፡ ይኖራል ። ... ፡ የንጹሓን ፡ መጕዳት ፡ አኹንም ፡ ለትንሽ ፡ ጊዜ ፡ ይቀጥላል ። ኾኖም ፥ ነገር ፡ ከልኩ ፡ አያልፍምና ፥ ብዙ ፡ ሳይቈይ ፡ የውንብድና ፡ ይዘቶቻቸውን ፡ ፍጻሜ ፡ እናያለን ❖

እግዚእናችንን ፡ የማስከበር ፥
ሕገ ፡ መንግሥታችንን ፡ የመሥራት ፥
ሥልጡንሕዝባዊ ፡ የርትዕ ፡ መንግሥታችንን ፡ የማቆም ፡

ሀገራዊ ፡ ዐላማችንን ፡ ለመፈጸም ፥ በኢትዮጵያና ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ የምንገኝ ፡ ሀገራውያን ፡ ኢትዮጵያውያን ፥ ሕዝባዊ ፡ አንድነታዊ ፡ አካላችን ፡ ለኾነው ፡ ለኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ እናብር!

የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት ።

ሥልጡንሕዝብና ።
www.slttunhzb.net


©ኢ..ሀ.ሥ.አ. ፥ 2016 ፡ ዓ.ም. ።